የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 እና 26

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ በስንት ብር ነበር?
ሀ)30 ለ)40 ሐ)50 መ)100

2. የካህናት አለቆች ጻፎች በማን ግቢ ተሰብስበው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው ይገድሉት ዘንድ ተማከሩ?
ሀ)ሐና ለ)ቀያፋ ሐ)ሊቀ ካህናቱ ግቢ መ)ለ እና ሐ

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሽቱ የቀባችዋ ሴት በየት ተቀምጦ ሳለ ቀባችው?
ሀ)በራሷ ቤት ለ)በማርታ እና ማርያም ቤት ሐ)በለምጻሙ ስምኦን ቤት መ)በዘኪዮስ ቤት

4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሽቱ የቀባችዋ ሴት ዋጋዋ ምን ነበር?
ሀ)ቁጣ እና መቅስፍት
ለ) ያደረገችው ስራ ወንጌል በሚነግርበት ቦታ መነገር
ሐ)ጌታችንን ዘወትር ማግኘት
መ)ሁሉም

5. እግዚአብሔር አበላነው አጠጣነው አለበስነው የሚባለው መቼ ነው?
ሀ) ለምስኪኖች ይህንን ሁሉ ስናደርገው
ለ) ለራሳችን ብቻ ካረግነው
ሐ) ለማንም ካላረግነው
መ) ሁሉም

6. በንጉሡ ግራ የቆሙት ፍየሎች ምን ፍርድ ተፈረደባቸው?
ሀ) ወደ ዘለዓለም እሳት እንዲሄዱ ተፈረደባቸው
ለ) የአባቴ ብሩካን ተባሉ
ሐ)ወደ ተዘጋጀላቸው መንግሥት ገቡ
መ)ሁሉም

7. በጎች እና ፍየሎች ብሎ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እና ማንን ነው?
ሀ) መላእክት እና ሰዎች ለ) አጋንንት እና መላእክት ሐ) ጻድቃን እና ሃጥአን መ)ሁሉም

8. ባለ አምስት መክሊት የሆነው በጎ አገልጋይ ሽልማቱ ምን ነበር?
ሀ)ወደ ጌታው ደስታ ገባ
ለ) ከሰነፍ አገልጋይ የተወሰደው አንድ መክሊት ተጨመረለት
ሐ) በብዙ ተሾመ
መ) ሁሉም

9. ከጌታው የተሰጠውን ወርቅ የቀበረው የትኛው ባለ መክሊት ነው?
ሀ) ባለ3 መክሊት ለ) ባለ ፣ መክሊት ሐ) ባለ 2 መክሊት መ) ባለ 5 መክሊት

10.በማቴ ምዕራፍ 25 አላውቃችሁም የተባሉት እነማን ናቸው?
ሀ)አስሩ ደናግል ለ) አምስቱ ልባም ደናግል ሐ) አምስቱ ሰነፍ ደናግል መ) ሁሉም ሰርገኞች

11. ሙሽራው በዘገየ ጊዜ ሁሉም ደናግላን ምን አደረጉ?
ሀ) መብራቶቻቸውን አበሩ ለ) ዘይት ሊገዙ ሄዱ ሐ) ነቅተው ጠበቁ መ)አንቀላፉ

12."ብራብ አብልታችሁኛል፣ ብጠማ አጠጥታችሁኛል፣ እንግዳ ብሆን ተቀብላችሁኛል፣ ብታረዝ አልብሳችሁኛል፣ ብታመም ጠይቃችሁኛል፣ ብታሰር ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛል። " እነዚህ ምን በመባል ይታወቃሉ?
ሀ) ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ለ) ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል ሐ) አንቀጸ ብጹዓን መ) ሕግጋተ ኦሪት

13.ቅዱስ ጴጥሮስ በንስሐ ያዘነው ሐዘን ከመጽሐፍ ቅዱስ አባቶች የማንን ይመስላል?
ሀ) ንጉሥ ዳዊት ለ) ይሁዳ ሐ) አዳም መ) ሀ እና ሐ

14."እረኛውን እገድለዋለሁ፣ በጎቹም ይበተናሉ" የሚለውን ትንቢት የተናገረው ማነው?
ሀ) ኢሳይያስ ለ) ዘካርያስ ሐ) አሞጽ መ) ንጉሥ ዳዊት

15.ጴጥሮስ በካህናት አለቃ ቅጽር ተቀምጦ ሳለ ብላቴናዋ የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን በምን አወቀች?
ሀ) በአለባበሱ ለ) በአነጋገሩ ሐ) ሐዋርያ መሆኑን ስለመሰከረ መ) ሀ እና ለ

16."ሁሉም ቢክዱህ እንኳ እኔ ከቶ አልክድህም " ያለው ሐዋርያ ማነው?
ሀ) ይሁዳ ለ) ዮሐንስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ስምዖን ቀነናዊ

17.ስርዓተ ቁርባን ስለምን በሥጋዴ እና በወይን ተደረገ?
ሀ) ጌታችን እና እመቤታችን ሲበሉ የኖሩት ሥጋዴ እና ወይን በመሆኑ ፍጹም ሥጋውን ፍጹም ደሙን እንደሰጠን ለማጠየቅ
ለ) ካህኑ መልከጼዴቅ በሥጋዴ እና በወይን ይሠዋ ነበርና
ሐ) ሥጋዴ ሥብ ሥጋ ይመስላልና ወይንም ትኩስ ደም ይመስላልና በመሰለ ነገር ለመስጠት
መ) ሁሉም

18.ምስጢረ ቁርባን ስለምን በመብል እና በመጠጥ ተደረገ?
ሀ) ምግብ እና መጠጥ ከሰውነት ይዋሃዳልና ፈጽሞ እንደተዋሃደን ለማጠየቅ
ለ) መብል እና መጠጥ ያፋቅራልና እንዳፈቀረን ለማጠየቅ
ሐ) ምድራዊ ምግብ በራበን ጊዜ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደን እንደልባችን እንድንበላ
መ) ሀ እና ለ

19.ከሚከተሉት ስለ ምስጢረ ቁርባን ሐሰት የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ጌታ ለሐዋርያት ብቻ ቁርባንን አቀበለ እንጂ ለራሱ አልተቀበለም
ለ) ይሁዳ ከዚህ ምስጢር ተካፍሏል
ሐ) ከትንሳዔ በኋላ የተፈጸመ ነው
መ) ሀ እና ሐ

20. ባለ አንድ መክሊቱ አገልጋይ የምን ምሳሌ ነው?
ሀ) ተምሮ ሌላውን የሚያገለግል
ለ) ተምሮ ሳያስተምር የቀረ
ሐ) መክሮ አስተምሮ ራሱን አስመስሎ የሚያወጣ
መ) መልሱ የለም